EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ቁጥር ፀጸ/16/15:2/14
ቀን ህዳር 06 2017

https://t.me/sirius_logistics

ለሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች
በሉበት

ጉዳዩ፡ LIBA Refined palm olein በመባል የሚታወቅ የምግብ ዘይት ምርትን ይመለከታል፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረዉ በብራንድ ስሙ LIBA በመባል የሚታወቅ እና ጅቡቲ ሀገር በሚገኘዉ GOLDEN AFRICA DJIBOUTI SARL አምራች የሚመረት የምግብ ዘይት ከዚህ በፊት Fortified ያልሆነ የምግብ ዘይትን ምዝገባ በማድረግ ምርትን በሀገር ዉስጥ ሲያስገበ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በሀገር ደረጃ ሁሉም የምግበ ዘይት Fortified መሆን እንዳለባቸዉ በተቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ሀገር ዉስጥም ሆነ ከዉጪ ሀገር ወደ ሀገር የሚያስገቡ የምግብ ዘይት አምራቾች ምርታቸዉን Fortified በማድረግ ምዝገባ በማካሄድ ምርታቸዉን እንዲያሰራጩ እየተደረገ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ድርጂት የሚያመርታቸዉን የምግብ ዘይት ምዝገባ እንዲያከናዉን ከዚህ በፊት የጊዜ ገደብ ተሰጥቷቸዉ ማስመዝገብ እንዳልቻሉ እንዲሁም የምርቱን ደህንነት እና ጥራት ለማረጋጋጥ የሚረዱ ወሳኝ የሆኑ ሰነዶችን በተደጋጋሚ እንዲያቀርቡ ቢጠየቁም ማቅረብ እንዳልቻሉ፣ በተለያዩ ጊዜያት የሚያቀርቧቸዉ ሰነዶች የተለያዩ ከመሆናቸዉ የተነሳ ጥርጣሬ እንዳደረበት እና የድርጅቱን ምርት መመዝገብ እንዳልተቻለ የምግብ መዝገባና ፈቃድ መሪ ስራ አስፈፃሚ በቢሮ ማስታወሻ ቁጥር ም/ም/ፋ/መ/ስ/አ/023/17 በቀን 06/03/2017 በተፃፈ አሳውቆናል፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ አንድ አንድ አስመጪዎች ይህ የገበያ ፈቃድ የሌለዉ ምርት ከአምራቹ በመግዛት ወደብ ላይ ጥያቄ እያቀረቡ እንደሆነ መረጃዎች እየደረሱን ሲሆን የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዳይሆን በስራችሁ የሚገኙ የምግብ አስመጪ ድርጅቶች እንዲሁም ለጉሙሩክ ፅ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በድብዳቤ በድጋሚ እንድታሳዉቁ እና ምርቶቹ ምዝገባ ሂደት ያልጨረሱ ስለሆነ፣ ምርቶቹን ወዳ ሀገር ማስገባት የማይቻል እና ወደ መጣባት ሀገር የሚመለስ እንደሆነና ኃለፊነቱን ያስ[illegible] ድርጂት የሚወስድ እንደሆነ እንድታሳዉቁ እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

EFDA
Ethiopian Food and Drug Authority
South east Addis Ababa Branch office

ግልባጭ
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለምግብ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር
- ምግብ ምዝገባና ፈቃድ መሪ ስራ አስፈፃሚ

ኢ.ም.መ.ባ

Tel . 251-11-552 4122/552 4123
ፋክስ/Fax: 251-11-552 1392
P.O.Box: 5681
Website: www.fmhaca.gov.et
E-mail: contactefda@efda.gov.et
IN REPLY REFER TO OUR REF. NO.
መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ